# ማሞ ምነ ቢሆን ነው፤



## አቡን ምን ቢነካው?



ማሞ ምነ ቢሆን ነው፤

አቡ ምን ቢነካው፤

ምን ክፉ ቢያገኘው፤

ለምን ይሆን አይኑ እንዲህ የፈጠጠው፤

እራሱን በእጆቹ አናንቆ የቀረው፤

እንዲህ መደንገጡ ክው ጭር ያለው?

ሃዘን አይነት አለው፤**የሞት**ም **ገጽታ**ው፤

እንደዚህ ደንግጦ በቁሙ የቀረው፤

ምን አይነት ጭካኔ ግፍ ቢውሉበት ነው፤

ገና በልጅነት ለጋ ወጣት ሳለው፤

እንደምን ስለምን እንደዚህ ይሁነው?

አይታየው ታይቶት፤

ከፊቱ ቆሞበት፤

**ጨካኙ ክፉ ምት፤**

ለምን አይደነግት ለምን ክው አይላት፤

ወንድሙን ከፊቱ በጥይት ነጥቀውት።

ሁለት ሺህ አምስት፤

በምርጫው ማግስት፤

ሽፍጠኞች በተንኮል ድምጹን ነጥቀውት፤

ሁሉ ተሰብስቦ አደባባይ ወጣት፤

በዚያ በድብልቅልቅ በዚያ ቀውጢ ሰአት፤

አላሚ ተኳሾች የወንድሙን ህይወት፤

በድንገት ሳያስብ ተኩሰው ነጠቁት።

ለምን አይደነግጥ፤

ለምን አይኑ አይፈጥ፤

ወንድሙ ከፊቱ በድንገት ሞቶበት፤

ሀዘኑ በርትቶ መላ ዘዴው ጠፍቶት፤

ጭንቅላቱ ፈርሶ ደሙን እያዘራ፤

ከፊቱ ተንጋሎ እሰትንፋሱ አጥራ፤

ለምን አይደነግጥ ለምንስ አይፍራ፤

ርህራሄ ባጣ በጭካኔ ስራ፤

ሞትን ከፊቱ ሲያይ በቀን በጠራራ።

ምን ክፉ አጋጣሚ ወንድም እህቶች፤

እንደወጡ መቅረት ባንጋች ታጣቂዎች፤

ከቤት ከየጎራው ከቀዬ አደባባይ፤

በግፍ ከየሜዳው ብዙ ወድቆ ሲታይ፤

ለነጻነት ዋጋ እንዲህ ተከፈለ፤

መታገል አልቆመም አሁንም ቀጠለ።

አቡም ዛሬ አድጓል፤

አመታት አልፈዋል፤

**የሆነውን ነገር እንደምን ይረሳል?**

**የነጻነት አርማ ችቦ ተቀብሏል፤**

**የአርነት አርማ ችቦ ተሸክሟል፤**

**ድልን ሰላበስር አልመለስ ብሏል።**

**ስንቱ ወድቆ ቀረ፤**

**ስንት ሺህ ታሰረ፤**

**ስንቱ ተሰደደ እንደወጣ ቀረ፤**

**ስንቱ ተሰቀየ ስንቱ ተወገረ፤**

**በግልጽና ስውር ፍዳው እየናረ፤**

**መከራ በዝቶበት ስንቱ ተመረረ፤**

**አማራጩን አጥቶ ህይወትን ገበረ፤**

**በያለበት ዛሬም ትግሉ ጠነከረ።**

**አስር አመት ይሁን ሰላሳ አርባም፤**

**ቢፈጥን ቢዘገይ ተዳፍኖ ቢመስልም፤**

**የአርነት ጉዳይ የቀናት አይደለም፤**

**የጭቆና ቀንበር ተሰብሮ እስኪያከትም፤**

**የክህደት ስርአት እስኪያበቃ ግፍም ፤**

**ትግሉ ይቀጥላል ነጻነት አይቀርም።**

**አቡ የሆነውን፤ ይጎብኙት ይህንን፤**

**አይጨፈንም አይን፤ መዝገቡ ያቆየው እንዲህ ነው ታሪኩን።**

http://www.maledatimes.com/wp-content/uploads/2012/07/Lideta-Anewar-mosq1.pdf

**ፍ.አ!**

07 29 2012